# የቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት አዋጅ

## መግለጫ

ኢመደአ

መጋቢት 2016 ዓ.ም

## ማውጫ

1) መግቢያ ........................................ 1

2) አዋጁ ያስፈለገበት ምክንያቶች ........................................ 3

3) ረቂቁን ለማዘጋጀት የታለፉ ሂደቶች ........................................ 4

4) የተወሰዱ ተሞክሮዎች ........................................ 5

5) የዋና ዋና ድንጋጌዎች ማብራሪያ ........................................ 6

6) ማጠቃለያ ........................................ 8

## 1) መግቢያ

ቁልፍ መሠረተ ልማት በአንድ ሀገር ግንባታ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ዋና አንቀሳቃሽ ሀብት ነው፡፡ ሀገራት ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ አፍስሰው ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን እየገነቡ ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግና የሀገር ሁለንተተናዊ እድገት ለማፋጠን ሲጥሩ ይስተዋላል፡፡ ቁልፍ መሰረተ ልማት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር ዕድገት ካላቸው የማይተካ ጠቀሜታ አንፃር ጉዳት በሚደርስባቸው ወይም በሚስተጓጎሉ ጊዜ በዜጎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ እንዲሁም በሀገር ብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ልዩና ጠንካራ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ እነዚህ ቁልፍ መሰረት ልማቶች ከሀገር ሀገር እንደ እደገት ደረጃው የተለያየዩ ቢሆኑም በዋናነት የማህበረሰብ አንቀሳቃሽ የሆኑትን የሀይል፣ የውሃና ተፋሰስ፣ የትራንስፖርት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ፣ የአደጋ ጊዜ፣ የጤና እንዲሁም የተለያዩ የመንግሥት አገልግሎቶችን አጠቃለው ይይዛሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ የቁልፍ መሰረተ ልማት አገልግሎትን ለመስጠት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በይበልጥ ጠቀሜታ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ ተቋማትም በአንድ ማዕከል በመተሳሰር ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ይህ ውህደት /Interoperability/ ታዲያ ለዜጎች ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ስጋትነቱ እየጨመረ ከመጣው የሳይበር ጥቃት ጋር በተያያዘ የራሱ የሆነ የደህንነት ስጋት ይዞ ብቅ ብሏል፡፡ በአንድ ተቋም ላይ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት ሌሎቹንም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ሊያቋርጥ፣ ሊያበላሽ፣ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊያወድም ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ከፍተኛ ጠቀሜታ ቢኖረውም ለጥቃት በሚጋለጥበት ጊዜ ከፍተኛ ውድመትና ኪሳራ ያስከትላል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ የጥቃቱ መድረስ እንኳን ከመታወቁ በፊት እጅግ ከፍተኛ ውድመት በቁልፍ መሰረተ ልማቱ ላይ ሲደርስ ይታያል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በቴክኖሎጂው የተሳሰሩ ተቋማት በአንድ ላይ ሊጎዱና ዜጎችም በአንድ ጊዜ ከበርካታ መገልገያ ተቋማት ጋር ሊቆራረጡ ይችላሉ፡፡

በቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እንደማንኛውም ጥቃት/physical attack/ በቀላሉ ለመከላከል አዳጋች ከመሆናቸውም በላይ በዘርፉ በርካታ ጥቃት አድራሽ አካላት መፈጠራቸውና በቴክኖሎጂ ታግዞ መከላከል ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ችግሩን ውስብስብ አድርገውታል፡፡ በተለይም ጥቃቱን ለመፈጸም ለጥፋተኞች አመቺ በሆነ ርቀት ላይ ሆኖ ማድረግ መቻሉ፣ ለድርጊቱ በአንፃራዊነት አነስተኛ ወጪና ሀብት የሚጠቀሙ መሆኑ፣ የህግ አስከባሪ አካላት በሳይበር ወንጀሎች መከላከልና ምርመራ ላይ የሚስተዋሉ የአቅም ክፍተቶች እንደ ትልቅ ተግዳሮት የሚዩ ሆነው ተለይተዋል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም በመስፋፋት ላይ የሚገኙት ቁልፍ መሠረተ ልማቶች መሠረታቸውን ኮምፒዩተርና ኮምፒዩተርን መሰረት ባደረጉ ስራዎች ላይ እየሆነ ይገኛል። እነዚህ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች እርስ በእርሳቸው እየተሳሰሩ መምጣት የዜጎችን የዕለት ተዕለት ኑሮ እያቀለለ መሆኑ እሙን ነው። በዚህም የተነሳ መሠረተ ልማቶቹ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መሠረት የሚያደርጉ በመሆናቸው ቁልፍ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚናቸው እየጨመረ እና ትልቅ ሀብትም እየሆኑ ይገኛሉ። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ መንግስት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በሰፊው ሀገራዊ የልማት አጀንዳ ውስጥ ያለውን አስተዋፅኦ ለማሳደግ የተለያዩ ኢኒሼቲቮችን (ዲጂታል 2025፣ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳ፣ የ10 ሀገራዊ ዕቅድ) ቀርፆ ወደ ስራ እየገባ ይገኛል። በዚህም እንደ ዲጂታል መታወቂያ፣ ሞባይል ክፍያ ፕላትፎርሞች፣ የሀገራዊ የኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት፣ ሲንግል ዊንዶ እና ሌሎችም መሰል መጠነ ሰፊ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ከፍተኛ መጠን ያላቸው ዳታዎች እየተሰበሰቡ ይገኛሉ። ይሁንና እነዚህ ትላልቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ዳታዎችና መሠረተ ልማቶች የቴክኖሎጂ ትስስራቸው እያደገ በሄደ ቁጥር እንደሌላው ዓለም ሁሉ ለስጋት የሚጋለጡበት መጠን እና የሚደርሰውንም ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ቀደም ብሎ ዝግጁነት የሚጠይቁ ናቸው።

ለአብነትም ሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቁልፍና የኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በከፍተኛ ደረጃ እያሻቀበ ይገኛል። በኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አስተዳደሩ ሪፖርት መሠረት በ2015 ዓ.ም ብቻ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን እና ተቋማትን ላይ ጨምሮ ወደ 6959 የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶች በሀገሪቱ ላይ መሞከራቸው አሳይቷል። ይህ አሃዝ በ2005 ዓ.ም ከነበረው አጠቃላይ 59 የሳይበር ጥቃት አንፃር ሲታይ ቁጥሩ በአሁኑ ወቅት በበርካታ እጥፍ ማደጉን መገንዘብ ያስችላል።

የመሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነትን ቁጥጥር ስርዓትን ለማሳለጥ ከሚወሰዱ የተለያዩ መንግሥታዊ እርምጃዎች ውስጥ የፖሊሲ ወይም የህግ ማዕቀፍ መፍጠር አንዱና ዋነኛው ነው። የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደርሰውን የሳይበር ስጋት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በግንባር ቀደምትነት ስልጣን ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት በአስተዳደሩ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 808/2006 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኢንፎርሜሽን እና ኮምፒዩተርን መሠረት ባደረጉ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደርሰውን አደጋ ከመከላከል አንፃር የሚያደርገው ተግባር አንዱና ዋነኛው ነው። በመሆኑም መንግስት የሀገሪቱን ዲጅታል አቅሞችን ለማሳደግና ለማስፋፋት የያዛቸውን እቅዶች ታሳቢ በማድረግ፤ ሀገራዊ የዲጂታላይዜሽን ጥረቱን ከሳይበር ደህንነት

አንፃር በመደገፍና በማረጋገጥ ረገድ ንቁ ተዋናይ ለመሆን የሚያስችል የቁልፍ መሰረት ልማቶች የሳይበር ደህንነት ጥበቃ አዋጅ ማውጣትና መተግበር ከምን ጊዜውም በላይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2) አዋጁ ያስፈለገበት ምክንያቶች

1) በኢትዮጵያ የተጀመሩ ዘርፈ ብዙ የዲጅታላይዜሽን ኢኒሼቲቮች ከምን ጊዜውም በላይ የሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲተሳሰሩ በማድረጉ፤ ከሳይበር ደህንነት አንፃር ተገቢው ጥበቃ ካልተደረገ ከፍተኛ የሆነ ጉዳትና ኪሳራ ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ፤

2) ከቴክኖሎጂ ዕድገትና የተደራሽነት መጠን መስፋፋት አንፃር በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚቃጡ የሳይበር ጥቃቶች ከዓመት ዓመት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመሩ መምጣቱ፤

3) የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሀገሪቱን ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት የማረጋገጥ ተልዕኮ ይዞ ቢቋቋምም፤ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ የጥበቃና ቁጥጥር የህግ ማዕቀፍ አውጥቶ ሳይተገብር መቆየቱ፤

4) ጉዳት ቢደርስባቸው በሀገር ጥቅምና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማቶች በህግ አግባብ አለመለየታቸው፤

5) በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ሀገራዊ ስጋትን ታሳቢ ያደረገ /risk based/ የሳይበር ደህንነት ጥበቃ እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ፤

6) የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ጥበቃና ቁጥጥር ስርዓት አስገዳጅ ለማድረግ የሚያግዝ ሁሉን አቀፍ ህግ ባለመኖሩ የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ እንዲሁም የኦዲት ሂደቶች በተቋማት ይሁንታ ላይ እንዲመሰረት ማድረጉ፤

7) ቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ክስተት በሚያጋጥማቸው ጊዜ መውሰድ ስለሚገባቸው አፋጣኝ እርምጃዎችና ከኢትዮ ሰርት እንዲሁም ሌሎች ተቋማት ጋር ማድረግ ስለሚኖርባቸው የሪፖርት አቀራረብና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ወጥና ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

8) የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችና የስልጠና ፕሮግራሞች ተቀርጸው ስራ ላይ ባለመዋላቸው በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች እና የኢንፎርሜሽን ደህንነት ባለሙያዎች ተገቢውን እውቀትና የእውቀት ሽግግር ማድረግ አለመቻላቸው፤

9) የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችና አስተዳዳሪዎቻቸው ላይ ግልጽ ተግባርና ኃላፊነት ማስቀመጥ ባለመቻሉ በተቋማት፣ በሀገር ጥቅምና ደህንነት ብሎም በዜጎች ላይ ለሚፈጠረው ጉዳት ወይም ተጽዕኖ ሃላፊነት የሚወስድ እና በህግ ተጠያቂ የሚያደርግ የቁጥጥር ስርዓት እንዲፈጠር ማድረጉ፤

10) ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነትን ከማረጋገጥ አንፃር ምርት እና አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋማት አለመኖር ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት ላይ ጫና ከመፍጠሩም በላይ በሀገሪቱ የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ኢኮ-ሲስተም እዳያድግ ማድረጉ፤

11) የቁልፍ መሰረተ ልማትን የሳይበር ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ የግል ተቋማትን ተሳትፎ በማጎልበት የቁጥጥር ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል ወጪና ኃላፊነትን ለመጋራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ናቸው።

## 3) ረቂቁን ለማዘጋጀት የታለፉ ሂደቶች

ይህንን ረቂቅ ለማዘጋጀት ሲታሰብ በቅድሚያ የተወሰደው እርምጃ በቁልፍ ኢንፎርሜሽን የሳይበር ደህንነት ጥበቃ እና ቁጥጥር ስርዓት ላይ አለም አቀፋዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታን በጥልቀት የሚዳስስ የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት ነው። ጥናቱ የቁልፍ መሰረተ ልማት ጽንሰ ሀሳብን ከቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ጋር በማነጻጸር የተነተነ ሲሆን ሀገራት የደረሱባቸውን የሳይበር ጥቃቶች ለመመከት ወይም ስጋት ለሆኑት ደግሞ የቅድመ መከላከል ስራ የሚሰሩበትን ብሎም የትብብርና የቅንጅት ስራዎችን የሚሰሩባቸውን ሁኔታዎችን ለይቷል። ጥናቱ በዋናነትም የቁልፍ መሰረተ ልማት ልየታ፣ ጥበቃና ቁጥጥር ስርዐትን አስመልክቶ በሀገራችን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመዳሰስ በተገቢው መንገድ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ስለሚለዩበት ሁኔታ፣ ስለሳይበር ደህንነት ፕሮግራምና የደህንነት ማዕቀፎች፣ ስለተቋማት ሃላፊነትና የአስገዳጅ ህግ ወይም ቁጥጥር ስርዓት ክፍተት መኖሩን አመላክቷል።

በዚህም መነሻነት ጥናቱ ይህን ችግር ሊፈታ የሚያስችል ቀደም ብለው የሚታወቁ የተቋምና የማዕቀፍ ስልጣኖችን ተፈጻሚ ሊያደርግ በሚችል መልኩ ማስተዳደር የሚችል ሁሉን አቀፍ ህግ እንዲወጣ እንዲሁም መደበኛ የሆኑ የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጉ ምክረሀሳብ አቅርቧል። ይህንን የጥናት ሪፖርት በተቋሙ ካሉ የሚመለከታቸው ክፍሎችና የበላይ አመራሮች ጋር በተዋረድ በመወያየት የተለያዩ ግብአቶች ከተሰጡ በኋላ የህግ ማዕቀፉ እንዲዘጋጅ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ረቂቁ ተሰርቷል።

በዚህ አግባብ የተዘጋጀውን ረቂቅ ሰነድ በተቋሙ ካሉና ከስራው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ካላቸው ክፍሎች ማለትም የሳይበር ፖሊሲ፣ ህግና ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ማዕከል፤ የሳይበር ደህንነት አስተዳደርና አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የሳይበር ደህንነት ግምገማና ፍተሻ ዲቪዢን፣ ከኢትዮ ሰርት እንዲሁም በዘርፉ ልምድና አቅም ያላቸውን ባለሙያዎች ጋር በመሆን ሰነዱን የማዳበር ስራ ተሰርቷል። በመቀጠልም በተሰጡ ግብአቶች መሰረት ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት የስራ ክፍሎች አመራሮች ጋር ተጨማሪ ውይይት በማድረግ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ አቅጣጫ የማስያዝ ስራ ተሰርቷል። በሂደትም ረቂቁን ለማዳበር የሚረዱ የንባብና የውይይት ስራዎችን በመስራት የዳበረውን ሰነድ ለተቋሙ የበላይ አመራሮች በማቅረብ አስፈላጊው ውሳኔ ከተሰጠበት ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የውጭ ባለድርሻ አካላት ጠርቶ በማወያየት ተጨማሪ ግብአት ይሰበሰባል።

## 4) የተወሰዱ ተሞክሮዎች

የዚህ ረቂቅ መነሻ የሆነው ጥናት ሲዘጋጅ በዘርፉ የተሻለ ተሞክሮ ያላቸው፣ በህግ ማዕቀፍና አደረጃጀታቸው ለግብአትነት የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮ ተዳስሷል። የሳይበር ደህንነት ለሁሉም የአለም ሀገራት ሁሉ እኩል ስጋት በመሆኑና ሀገራትም በተጠንቀቅ የሚቆሙበት ጉዳይ እየሆነ በመምጣቱ የሚወስዷቸውንም የሳይበር ደህንነት እርምጃዎች፣ የህግ ማዕቀፎችና ተቋማዊ አደረጃጀቶች በግልጽ ለሌላ አካል ተደራሽ ከማድረግ ስመሊቆጠቡ በተፈለገው መጠን መረጃዎችን ለመሰብሰብ እክል ፈጥሮ ነበር። ሆኖም በተሻለ ሁኔታ የህግና የአሰራር ስርዓታቸውን ማግኘት የተቻሉ ሀገራት የጋና፣ ሞሪሸስ፣ አውስትራሊያ፣ ኮሪያ እና የሲንጋፖር ተሞክሮ ተዳስሷል። እነዚህ ሀገራት የተመረጡት የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትን ከመለየት፣ ከመሰየም እንዲሁም ጥበቃና ቁጥጥር ስርዓት ከመዘርጋት አንጻር የተሻለ የህግ ማዕቀፍ፣ ተቃማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት በተሻለ ሁኔታ በመዘርጋታቸው ነው። እነኚህ በጥናቱ የተዳሰሱ ቢሆንም በተጨማሪነት ለረቂቅ ዝግጅቱ በግብአትነት ይውላሉ ተብለው የታሰቡ የተለያዩ ሀገራት ድንጋጌዎችን በማየት የረቂቁ ክፍሎች ተዋቅረዋል።

በተሞክሮነት ከታዩት ሀገራት ለረቂቁ ጥሩ ግብአት ይሆናሉ ተብለው የተለዩትና በዝግጅቱ ወቅትም የተካተቱ ነጥቦች የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን መለየትና ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን በህግ መለየት፣ የቁጥጥር ስርዓትና አደረጃጀት መዘርጋት፣ የቁጥጥር ስርዓቶች ተግባራዊነትን ከመከታተልና አስገዳጅ ድንጋጌዎችን ማስቀመጥ፣ የሳይበር ክስተት ምላሽ መስጫ ማዕከላትን ማቋቋምና ሪፖርት ማድረግ፣ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ማበጀት፣ ፈንድ በማቋቋም የጋራ ወጪን ከመጋራት፣ የቅድመ ልምምድ ማድረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን መፍጠር የመሳሰሉት ናቸው። በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከነበሩ ማዕቀፎች የአስገዳጅነት ሚና ባይኖራቸውም እስካሁን ሲያሰሩ የነበሩትንና በቀጣይም

ህጉ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገቡ ስታንዳርድና የአመራር ስርዓት ተብለው የተለዩ ሰነዶችን ሀሳቦች በመግዛት በረቂቅ ህጉ ለማካተት ተሞክሯል።

## 5) የዋና ዋና ድንጋጌዎች ማብራሪያ

የህግ ረቂቁ የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትን ለመደንገግ በሚያስችል መልኩ በረቂቅ ስድስት ክፍሎች እና በ31 አንቀጾች ተዋቅሯል። በክፍል አንድ በተለመደው የህግ አቀራረጽ የትርጓሜ ክፍልንም የሚያካትት ሲሆን በተለይም ስለ  ለቁልፍ መሰረተ ልማት የተቀመጠው ትርጓሜ በአዋጁ ሊነሱ የተፈለጉ ሀሳቦችን በሚያካትና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩዊ ትርጉም እንዲይዝ ተደርጓል።  የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት አስተዳዳሪ በሚል የተተረጎመው ቃል በዚህ ህግ ውስጥ የመንግስትም ሆኑ የግል መሰረተ ልማቶች ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ተብለው ሊለዩ ስለሚችሉና በዚህ ህግ ስለሚተዳደሩ እነዚህም መሰረተ ልማቶች በባለቤትነትም ሆነ በማናቸውም አኳሃን ሃላፊነት ወስዶ የሚያስተዳደር የግል ባለሀብት ወይም ባለሙብት እንዲሁም የመንግስት መሰረተ ልማቶችን የማስተዳደር ሃላፊነት የተሰጠው ሰው በዚህ ህግ የተቀመጡትን ሙብትና ግዴታዎች የማክበር ግዴታ እንደሚኖርበት ለማመላከት ነው።

በዚህ ክፍል ያለው ሌላኛው ጉዳይ የተፈጻሚነት ወሰን ሲሆን አዋጁ የኢትዮጵያ ቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች እና ለቁልፍ መሰረተ ልማቱ የሳይበር ደህንነት ምርት እና አገልግሎት ለሚያቀርቡ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ይገልጻል። ይህም  የሚመለከተው የሳይበር ደህንነት ጥቃትንና ጥበቃን እንደመሆኑ በዚህ ህግ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተብለው የሚለዩና በኢትዮጵያ ግዛትና ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ እንዲሁም የሀገሪቷ ህግ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ቦታዎች ሁሉ በሚገኙት ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶች ላይ በሙሉ ተፈጻሚ እንደሚሆን ለማሳየት ነው። በተጨማሪም ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በመንግስት አቅም ብቻ መስጠት አዳጋች ከሆኑም በላይ የግል ዘርፉ የሳይበር ደህንነትን በማረጋገጥ ረገድ ያለውን ሚና ለማሳደግ በማሰብ ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ፈቃድና እውቅና መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ አዋጁ በነዚህ አካላት ላይም ተፈፃሚ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

በክፍል ሁለት በዋናነት የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ከመለየት እና ደህንነታቸውን ከማስጠበቅ አንፃር የተቃኙ አንቀፆች ተካተዋል። በአንቀጽ 4 አስተዳደሩ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን እንደሚለይ የተቀመጠው ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት ልየታው የሚከናወነው ማንኛውንም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት የሚጠቀሙ መሰረተ ልማቶች የሚደርስባቸው ጥቃት የሚያስከትለውን ሀገራዊ ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ይሆናል። በተጨማሪም በዚህ ክፍል ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ባለቤቶች ወይም

የሚያስተዳድሩ አካላት የሳይበር ደህንነትን ከማረጋገጥ አንፃር ሊወስዷቸው የሚገቡ እርምጃዎች በዝርዝር እንዲመላከቱ ተደርጓል። በዚህ ክፍል የመጨረሻ አንቀፅ 8 ላይ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎቶችን በአዋጁ መሰረት እውቅና እና ፈቃድ ተሰጥቷቸው በሚንቀሳቀሱ የግል ተቋማት ማግኘት የሚችሉበት አማራጭ የተከፈተ ሲሆን ይህም የግል ዘርፉን ከማበረታት ባለፈ ውስን አቅም ያላቸው የቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት በአዋጁ የተቀመጡ ግዴታዎችን በሦስተኛ ወገን በአነስተኛ ወጪ ተጠያቂነት በሰፈነበት መልኩ ለማከናወን ዕድል ይሰጣቸዋል። ሆኖም ከዚህ ጋር ተያይዞ አስተዳደሩ ከሚይዙት መረጃና ከሚያስተዳድሩት ሀብት አንፃር ከፍተኛ የሆነ የሀገር ደህንነት ስጋት የሚፈጥሩ በመሆናቸው ምክንያት በውክልና የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ማግኘት የማይችሉ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ለይቶ የማሳወቅ ኃላፊነት ተጥሎበታል።

ክፍል ሶስት ስለ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራም የሚደነግግ ሲሆን በዚህም በዋናነት የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር የአስተዳደሩ ዋና ዋና ኃላፊነቶች ተመላክተዋል። በቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትነት የሚለዩ ተቋማት መከተል እና ማልማት ስለሚኖርባቸው ስለሚኖርባችው የሳይበር ደህንነት አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ የሳይበር ክስተቶች ምላሽ አሰጣጥ ስርዓቶች፣ እንዲሁም ከሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ፍተሻና ግምገማ አንፃር መከተል ስለሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች እና ሂደቶችን ይዘረዝራል። የአዋጁ ክፍል አራት ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋማትን እና ባለሙያዎችን ፈቃድ እና እውቅና ስርዓቶች ይደነግጋል። በዚህም የፈቃድን አስፈላጊነት፣ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ጥቅል መስፈርቶችን፣ ፈቃድ የሚታደስባቸውን አግባቦች፣ ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ግዴታ፣ ፈቃድ ስለሚሰረዝባቸውና የሚታገድባቸው አግባቦች በዝርዝር ይዟል።

ክፍል አራት በመንግሥት ውስን ፋይናንስ አቅም ብቻ ሊፈፀሙ የማይችሉ የቁልፍ መሰረተ ልማቶቸን ደህንነት ማስጠበቅ ተግባራት ለመደገፍ የሚያስችል ፈንድ አቋቁሟል። ፈንዱ በዋናነት የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን ለመተግበር፣ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ለመደገፍ፣ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት፣ የስልጠና እና አቅም ግንባታ ተግባራትን ለመደገፍ እንዲሁም ከአስተዳደሩ ውጪ በተለያዩ ግለሰቦች የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ተግባራትን ለመደገፍ በሚውል መልኩ ተዘጋጅቷል። ፈንዱ የተለያዩ ምንጮች አንዲኖሩት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በዋናነት ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የሚያደርጉት መዋጮ፣ ከተለያዩ አካለት የሚገኙ ገቢዎች እንዲሁም አስተዳደሩ አዋጁን በማስፈፀም ሂደት ከሚያቀርባቸው አገልግሎቶች እንዲሁም ከቅጣት የሚሰበሰቡ ወጪዎች የፈንዱ ምንጮች ሆነው ተደንግገዋል። የፈንዱን አስተዳደር አስመልክቶ ከመንግስት በሚሰጥ አቅጣጫ

መሰረት በአስተዳደሩ የሚተዳደር ሲሆን ዝርዝር የፈንዱ አሰራር ስርዓት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን ተመላክቷል፡፡

ክፍል አምስት ለቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ስለሚሰጥባቸው ዝርዝር ጉዳዮች ይዞ ተዘጋጅቷል፡፡ በክፍል ስድስት  ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የሰፈሩ ሲሆን የመተባበር ግዴታ፣ አስተዳደራዊ እርምጃና የወንጀል ቅጣቶች የተቀመጡበት አብዛኛው የህጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት በተቋማት ላይ እንደመሆኑ መጠን ህጉን ጥሰው በሚገኙት ላይም ከማስጠንቀቂያ እስከ የተለያዩ መጠን የገንዘብ ቅጣት ድረስ ተጥሎባቸዋል፡፡ ከዚህም በተረፈ ተቋማቱን በሚያስተዳድሩ ወይም በሃላፊነት በሚመሩ ሰዎች ላይ የወንጀል ተጠያቂነትን መፍጠር በህጉ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በአጽንኦት እንዲፈጸሙ ከመርዳቱም በላይ ለህጉ ተፈጻሚነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ይወጣል፡፡ ይህም በተሞክሮነት በተወሰዱ ሀገራት ህጎች ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ለቅጣት መጠን መለኪያነት የተወሰደው ተመሳሳይነት ካላቸው የተለያዩ ሀገራችን ህጎች ላይ የተቀመጡ የቅጣት መጠኖች ሲሆን በዚህ ህግ በዋናነት መሰረት የተደረገው በቁልፍ ተቋማቱ የዳታ ደህንነት፣ የተቋማቱን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አንጻር (business continuity) እንዲሁም ተቋማቱ ከሌሎች ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር መጠን(dependency) እና ያንንም ተከትሎ የሚደርሰው ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## 6) ማጠቃለያ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በአዋጅ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል አንዱ የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ብሔራዊ የፖሊሲ፣ የህግ፣ የስታንዳርድ እና ስትራቴጂ ረቂቆችን የማዘጋጀትና ሲጸድቁም ተፈጻሚነታቸውን የመከታተል ብሎም መንግስታዊ እና የግል ተቋማት አገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ማዕቀፎችን ተከትለው የየራሳቸው ፖሊሲና ስታንዳርድ እንዲቀርጹ ያስገድዳል፤ ይህም ከዚህም ቀደም ብሎ በመውጣት በስራ ላይ መዋል የነበረበት ህግ መሆኑን ያሳያል፤ ይህም ባለመሆኑ በተቋሙ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የቁጥጥር ስራ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ጉዳዩን የሚመራ አስገዳጅ ህግ ባለመኖሩ በተገቢው መንገድ ለማስፈጸም ተግዳሮቶችን ፈጥሯል፡፡ ወቅቱ ከደረሰበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እድገትና ውስብስብነት አንጻር ብሎም የሳይበር ጥቃት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመርን ተከትሎ የህጉ አለመኖር የችግሩን አሳቢነት ያጎላዋል፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ሀገራችን የሳይበር ደህንነት ዙሪያ የወጡ አለም አቀፍም ሆነ አህጉራዊ ስምምነቶች ላይ አባል ባትሆንም ወይም እስካሁን ያጸደቀችው ሰነድ ባይኖርም ዘመኑ ከደረሰበት

የቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዞ መሰል ጉዳዮችን ለማስተዳደርና አለምአቀፋዊ የቅንጅትና ትብብር ስራዎችን ለመስራት መሰል ጉዳዮችን ማስተናገድ ስለምትችልበት አግባብ ማሰብ ያስፈልጋል። በዚህ ዙሪያ ለሚኖር እንቅስቃሴ አገር አቀፍ ሁኔታውን ለመግዛት አሁን በመረቀቅ ላይ ያለው ህግ የጎላ ሚና ይኖረዋል።

በመሆኑም ህጉ የቁልፍ ኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማትን የሳይበር ደህንነት ከመጠበቅና ተቋማቱ ያለባቸውና ሃላፊነት፣ መንግስት ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሚያደርጋቸውን ጥበቃዎችና የሚጥላቸውን ግዴታዎች፣ የሳይበር ኦዲት ፍተሻና ግምገማ ስርዓት ፣እንዲሁም በህጉ የተመላከቱ ድንጋጌዎችን በማያከብሩ አካላት ላይ ስለሚወሰዱ ተመጣጣኝ እርምጃዎች ለማሳወቅ በሚያመች መልኩ ተቀርጿል። ይህም ረቂቅ ህጉ ጸድቆ ወደ ትግበራ ሲሸጋገር የሀገሪቱን ዲጂታላይዜሽን ኢኒሼቲቮች ደህንንነት በማረጋገጥ የሀገርን ደህንነትና የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማስጠበቅ በጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

**አዋጅ ቁጥር …. /2016**

# የቁልፍ መሠረተ ልማቶች ሳይበር ደህንነት አዋጅ

በቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶች በሀገሪቱ ምጣኔ ሃብት፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ሉዓላዊነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ በመሆናቸው፤

በሀገራዊ የዲጂታላይዜሽን ሽግግር አማካኝነት በሀገራችን ቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና መሰረተ ልማቶቹ የሚይዟቸው መጠነ ሰፊ መረጃዎችና ዳታዎች ላይ እየጨመሩ የመጡ የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶችን መቀነስና መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለቁልፍ መሠረተ ልማቶች ስጋትን መሠረት ያደረገ ልየታ በማድረግ የሀገሪቱን ሀብት አቀናጅቶ ለመጠቀምና አይበገሬነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሳይበር ደህንነት ጥበቃና ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ጥበቃ በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ፣ ውጤታማና ፈጣን የመረጃ ልውውጥ እና የሳይበር ክስተቶች ለማጋራትና ለመግታት የሚያስችል ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ውስብስብ፣ ተለዋዋጭ እና ከፍተኛ የሆነ ወድድር ባለበት የሳይበር ምህዳር ውስጥ የሚደረግ የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ተግባር ከፍተኛ የሆነ የካፒታል አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ለቁልፍ መሠረተ ልማቶች ጥበቃ የሚውል አስተማማኝ ሀገራዊ የፋይናንስ አቅም መፈጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን በሚያስተዳድሩና የሳይበር ደህንነት ጥበቃን በሚያደርጉ አካላት ላይ ግልፅ ኃላፊነትና ግዴታ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት አዋጅ ቁጥር … /2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፤

1/ **“ቁልፍ መሰረተ ልማት”** ማለት ለጥቃት ከተጋለጡ በህዝብ ደህንነትና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ መሰረተ ልማቶች ወይም ተቋማትን ያካትታል፤

2/ **"የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት"** ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች፣ አገልግሎቶች፣ ኔትወርኮች፣ የአሰራር ስርዓቶች፤ ሶፍትዌር መተግበሪያዎች ስልተ ቀመሮች ያካትታል፤

3/ **"የሳይበር ምህዳር"** ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ ልማቶች፣ መረጃ ስርዓቶች፣ መረጃን ወደ እውቀት የሚቀይርና የሚጠቀም የሰው ሃይል፤ እንዲሁም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህል ያካተተ ምናባዊ ባህሪ ያለው ምህዳር ነው።

4/ **"ጥቃት"** ማለት በሳይበር ምህዳር የሚፈጸም ቁልፍ መሰረተ ልማት የማስተጓጎል፣ ያለፈቃድ ብርበራ፣ የመረጃ ስርቆት፣ ስነ ልቦናዊ ጦርነት እና ሌሎችም አይነት በምህዳሩ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ያካትታል።

5/ **"የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት"** ማለት ህጋዊ የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት ወይም በቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤቱ መሰረተ ልማቱን እንዲያስተዳደሩ የተወከሉ ሰዎችንም ይጨምራል፤

6/ **"የሳይበር ደህንነት ፕሮግራም"** ማለት በአደጋ ትንተና ላይ የተመሰረተ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲተገበሩ የሚወጡ ስትራቴጂያዊ፥ የታክቲክ እና ኦፕሬሽናል እና የአሠራር እርምጃዎች እንዲሁም የአስተዳደር መዋቅሮችን ያጠቃልላል፤

7/ **"የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ"** ማለት አስተዳደሩ ወይም ቁልፍ መሰረተ ልማቶች እንዲያወጧቸው የሚጠበቁ የሳይበር ደህንነትን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ፣ የአተገባበር፣ የሂደት፣ የአሰራር ስርዓት፣ የስልት እና ሌሎች መሰል ሀገራዊ ወይም ዘርፍ ተኮር አስገዳጅ ወይም አስገዳጅ ያልሆኑ ማዕቀፎች ናቸው፤

8/ **"የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ"** ማለት በሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች መሠረት ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን የቅድመ ልማት፣ ቅድመ ግዥ እና ቅድመ ትግበራ ላይ የሚደረግ ፍተሻ እና ግምገማ የማድረግ ተግባር ነው፤

9/ **"የደህንነት ማረጋገጫ"** ማለት አንድ ሰው ለታጨበት ወይም ለተመደበበት የስራ ሃላፊነት፣ ታማኝነትና አስፈላጊ ስብዕና ያለው መሆኑን የማጥናትና የማጣራት ሂደት ነው፤

10/ **"የሳይበር ደህንነት ኦዲት"** ማለት በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ተጋላጭነትን ለማወቅ የዘልቆ ገብ ፍተሻ ተግባራትን ማከናወን እና ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ስርዓት በመገምገም እንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረግን ይጨምራል፤

ረቂቅ

11/ **"የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

12/ **"የሳይበር ደህንነት ባለሙያ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሳይበር ደህንነት ተግባራትን እንዲያከናውን እውቅና የተሰጠው ሰው ነው፤

13/ **"አስተዳደር"** ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነዉ፤

14/ "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፤

15/ ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተብለው በተለዩ መሰረተ ልማቶች እና ለቁልፍ መሰረተ ልማቶቹ የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎት በሚያቀርቡ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ስለመለየትና ስለመጠበቅ

4. <u>ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ስለመለየት፤</u>

1/ አስተዳደሩ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ የሀገሪቱን ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ይለያል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ቁልፍ መሠረተ ልማትን ለመለየት የሚከተሉት ዝቅተኛ መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፦

ሀ) የሳይበር ጥቃት ቢደርስበት በምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚጥል ሲሆን፤

ለ/ የሳይበር ጥቃት ቢደርስበት በብሔራዊ ደህንነት፣ በሰላምና መረጋጋት፣ በዲፕሎማሲ ወይም ሀገራዊ ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሲሆኑ፤ ወይም

ሐ) ከፍተኛ ትስስርና መስተጋብር ያላቸውና ጉዳት ቢደርስበት ወደ ሌሎች ዘርፎች የሚዛመት ሲሆኑ።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፤ አስተዳደሩ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶች በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

4/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ መሠረት ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ሲለይ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት

በማድረግ፤ የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነት ስጋት ተፅዕኖ መተንተንና መገምገም እንዲሁም ወቅታዊ ፍላጎትን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

## 5. ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ስለመሰየም

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 መሠረት የለያቸውን ቁልፍ መሠረተ ልማቶች በመመሪያ ይሰይማል።

## 6. ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ስለመሰረዝ

1/ ቁልፍ መሠረተ ልማት ተብሎ የተሰየመ መሰረተ ልማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4(2) ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ሲያቆም አስተዳደሩ ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ሊሰርዝ ይችላል፤

2/ ከቁልፍ መሰረተ ልማትነት ለተሰረዘ መሰረተ ልማት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደረገው ጥበቃ ይቋረጣል።

## 7. የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት ግዴታ

ማንኛውም የቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ የራሱን የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን የመቅረፅ፤

2/ በአስተዳደሩ የሚወጡ ወይም እውቅና የተሰጣቸውን አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች ተግባራዊ የማድረግ፤

3/ በአስተዳደሩ የሚወጡ ፖሊሲና ህጎችን መሠረት ያደረገ የራሱን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ማዘጋጀትና ተግባራዊ የማድረግ፤

4/ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ቁልፍ ሀብቶች፣ ዳታዎች እና መረጃዎችን የመመደብና የመጠበቅ፤

5/ በስትራቴጂ፣ ታክቲክ እና ኦፕሬሽን ደረጃ ወቅታዊ የሳይበር ደህንነት የአደጋ ዳሰሳ እና የተፅዕኖ ትንተና ማድረግ፤

6/ አስተዳደሩ በየአመቱ በሚያከናውነው ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት የአደጋ ዳሰሳ ላይ የመሳተፍና አስፈላጊ መረጃዎችን የማቅረብ፤

7/ በአስተዳደሩ የሚሰጠውን የሳይበር ኦዲት እና የሳይበር ፍተሻና ግምገማ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመያዝና ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የማሳደስ፤

8/ አስተዳደሩ በሚያደርገው የሳይበር ኦዲት ወይም የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ግኝት መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ የመውሰድ፤

9/ በሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ መሠረት አስፈላጊውን የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት የመፍጠር፣ በጀት የመመደብ፣ ከአስተዳደሩ የሰጣቸው ወይም

የተቀበላቸው የሙያ ሰርተፍኬት ያገኙ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን የመቅጠር፤

10/ ጥቅም ላይ የሚያውሏቸውን የቴክኖሎጂ ምርቶች አቅርቦት ሰንሰለት ደህንነት ማረጋገጥ እና አዳዲስ ወይም ተሻሽለው የሚቀርቡ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በግዥ፣ በስጦታ፣ በማልማት ወይም በማንኛውም መልኩ አግኝተው ከመተግበራቸው በፊት ከአስተዳደሩ የሳይበር ደህንነት ማረጋገጫ የማግኘት፤

11/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት የሳይበር ጥቃቶችን ክትትል፣ ሪፖርት እና ምላሽ የማድረግ፤ ክስተት ማጋጠሙን እንዳወቁ በ48 ሰዓት ውስጥ አስተዳደሩ በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት የማሳወቅ፤ እና የሚሰጣቸውን መፍትሔዎችና አቅጣጫዎችን የመተግበር፤

12/ አስተዳደሩ በሚዘረጋው የመረጃ መለዋወጫ ስርዓት ተጠቅሞ በየወቅቱ አስፈላጊ መረጃ የመለዋወጥ፤

13/ የሳይበር ደህንነት ልምምድና ስልጠና ፕሮግራሞችን የማዘጋጀትና የመተግበር እንዲሁም አስተዳደሩ በሚያመቻቻቸው ልምምድና ስልጠናዎች ላይ የመሳተፍ፤

14/ የቁልፍ መሠረት ልማቱ ወሳኝ የሆኑ ሀብቶች ተደራሽነት የሚሆኑላቸው ሰራተኞችን በሚመለከተው የመንግሥት አካል የደህንነት ማረጋገጫ እንዲያገኙ የማድረግ፤

15/ የሳይበር ደህንነት የሚጠይቀውን የሙያ ስነ-ምግባር መከበሩን የማረጋገጥ።

## 8. <u>ውክልና ስለመስጠት</u>

1/ ቁልፍ መሰረተ ልማት ባለቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 የተደነገጉ ግዴታዎች እንደአግባብነቱ በራሱ አቅም ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የሳይበር ደንነት አገልግሎት በሚያቀርብ ሰዎችን ውክልና በመስጠት ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አስተዳደሩ ከብሔራዊ ደህነትና ጥቅም አንፃር በውክልና የሳይበር ደህንነት አገልግሎት የማይሰጥባቸውን የቁልፍ መሰረተ ልማቶች በመመሪያ ይለያል።

## ክፍል ሦስት
## የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ሳይበር ደህንነት ስርዓት

## 9. <u>ስለሳይበር ደህንነት አስተዳደር</u>

አስተዳደሩ፡-

1/ አስገዳጅ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፤ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

2/ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሚያወጧቸው የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞች፣ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍን ተከትለው መዘጋጀታቸውንና መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

3/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ትግበራ ሂደትን ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፣

4/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት አደጋ፣ የብስለትና የደህንነት ቁመና ዳሰሳ ሪፖርት በየዓመቱ ያዘጋጃል፣

5/ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የሳይበር ደህንነት ልምምዶችን፣ ስልጠናዎችን እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን የማዘጋጀትና የመተግበር፣

6/ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትና አይበገሬነት ለመፍጠር የሚያስችል ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ደህንነት ፎረም ይመሰርታል፣ ያስተዳድራል፣

7/ የሚያወጣቸውን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ አስፈላጊ መረጃዎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተደራሽ ያደርጋል።

## 10. <u>ስለሳይበር ክስተቶች ምላሽ አሰጣጥ</u>

አስተዳደሩ፦

1/ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ ጥቃቶች እንዳይደርሱ ተገቢውን የቅድመ መከላከል እና ጥቃቶች ሲደርሱ ምላሽ የሚሰጥበትን መመሪያ ይዘረጋል፣

2/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሳይበር ጥቃቶች ለመከላከል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

3/ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ክስተቶች የመረጃ ልውውጥና የቅድመ ማስጠንቀቂያ በመመሪያ ይዘረጋል፣

4/ የሳይበር ክስተቶችን በመከላከል ዙሪያ ሀገር አቀፍ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ የትብብርና የትስስር ግንኙነቶችን ያስተባብራል በበላይነት ይመራል፣

5/ በቁልፍ መሰረተ ልማት የሚቋቋሙ የደህንነት ኦፐሬሽን የዘረጓቸውን የአሰራር ስርዓቶች እና አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመመሪያ ይዘረጋል።

## 11. <u>የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ</u>

አስተዳደሩ፡-

1/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን ቢያንስ በየዓመቱ መደበኛ እና በማንኛውም ጊዜ ድንገተኛ የሳይበር ደህንነት ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፣ የሳይበር ደህንነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣

2/ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን እና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ያደርጋል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 እና 2 መሠረት የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማዎችን እንዲያደርጉ መመሪያ በማውጣት ለግል አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፣

4/ የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣ ሰርተፍኬቱ ስለሚሰጥበት እድሳት ስለሚደረግበት አግባብ በመመሪያ ይወስናል፣

## 12. ስለ አገልግሎት ክፍያ

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያዎችን ይሰበስባል።

## ክፍል አራት
## ስለፈንድ መቋቋም

## 13. መቋቋም

1/ የቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ፈንድ ከዚህ በኋላ “ፈንድ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

2/ ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለፈንዱ ዓላማ ማስፈፀሚያ ይውላል፡፡

## 14. የፈንዱ ዓላማዎች

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1/ የቁልፍ መሰረተ ልማት ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ተጨማሪ ሃብት የሚገኝበትን አሰራር በመፍጠር በመንግሥት ውስን በጀት ሊሸፈኑ የማይችሉ የሳይበር ደህንነት ሥራዎችን መደገፍ፣

2/ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ በአስተዳደሩ የሚዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ፕሮግራሞችን እና የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን ለማስተገበር የሚያስችል ድጋፍ ለማድረግ፣

3/ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ተግባራትን መደገፍ፣

4/ የቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የስልጠና እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ለመደገፍ፤

5/ ቁልፍ መሰረት ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ ለሚፈፀሙ ተግባራት እና ሥራውን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የሚያግዙ አስቻይ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት፤

6/ በቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት መካከል ወቅታዊ የሳይበር ደህንነት ልምምዶችን በቅንጅት ለማድረግ፤ እና

7/ የቁልፍ መሠረት ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ በግለሰቦች፣ በቡድኖች ወይም በማህበረሰቦች ተነሳሽነትና በጎ ፈቃደኝነት የሚከናወኑ ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ማስተባበር።

## 15. የፈንዱ ምንጭ

1/ የፈንዱ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ለሳይበር ደህንነት ከሚይዙት በጀት ላይ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ተወስኖ የሚያዋጡት ዓመታዊ መዋጮ፤

ለ. ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ ከተለያዩ ተቋማትና አጋር ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች የሚገኙ እርዳታና ድጋፎች፤

ሐ. በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰቡ የአገልግሎት ክፍያዎችና ከቅጣት የሚሰበሰቡ ገቢዎች፤

መ. ከተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያና መሰል ፕሮግራሞች የሚገኙ ገቢዎች፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) መሠረት በፕሮጀክት የሚገኙ የፋይናንስ ድጋፎች ካሉ በፕሮጀክቱ ሰነድ ወይም ድጋፉን ካደረጉ አካላት ጋር በሚደረግ የስምምነት አግባብ የሚፈጸሙ ይሆናሉ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተገኘው ገንዘብ ለፈንዱ ሲባል በገንዘብ ሚኒስቴር በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ይደረጋል፤ ፈንዱ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ ይኖረዋል፡፡

## 16. የፈንዱ ተሰብሳቢ ገቢ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአስተዳደሩ የሚሰበሰቡ ገቢዎች በየወሩ መጨረሻ ለፈንዱ ገቢ ይሆናሉ፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አስተዳደሩ ገቢ ማድረጉን በ7 /ሰባት/ ቀናት ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያሳውቃል፡፡

## 17. ከፈንዱ ለመጠቀም የሚያበቁ መመዘኛዎች

የፈንዱ አጠቃቀምን በሚመለከት ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 18. ስለ ፈንዱ ሂሳብ

1/ ጽህፈት ቤቱ የፈንዱን ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

2/ የፈንዱ ሂሳብ በየዓመቱ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚሰየሙ የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፤

3/ የሂሳብ ምርመራዎችና ሌሎች የፋይናንስ ዘገባዎች በገንዘብ ሚኒስቴሩ በፀደቁ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ይደረጋሉ፡፡

## 19. ስለፈንዱ አስተዳደር

1/ ፈንዱ መንግሥት በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት በአስተዳደሩ በሚቋቋም ፅሕፈት ቤት ይተዳደራል፤

2/ የፈንዱ ዝርዝር የአሰራር ስርዓት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

# ክፍል አምስት
# ስለሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪዎች

## 20. ለሳይበር ደህንነት አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ

1/ አስተዳደሩ የሳይበር ደህንነት አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ ይሰጣል፤

2/ ማንኛውም የሳይበር ደህንነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአስተዳደሩ የሚሰጠውን ፈቃድ ሳይኖረው የሳይበር ደህንነት ምርት ወይም አገልግሎቶችን መስጠት አይችልም፤

3/ አስተዳደሩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የሳይበር ደህንነት ምርትና አገልግሎት ዓይነቶችን፣ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ሥርዓት፣ ስለፈቃድ ይዘት፣ ምላሽ ስለሚሰጥበት፣ ፍቃድ ስለሚታደስበት ስለቅሬታ ስለሚቀርብበት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝሩን በመመሪያ ይወስናል።

## 21. ፈቃድ የሚሰጥባቸው ዋና መስፈርቶች

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 17 መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፦

1/ የነዋሪነት መታወቂያ፣ ዲጂታል መቃወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የሕግ ሰውነት ማረጋገጫ ሰነድ፤

2/ ተገቢውን የደህንነት ማረጋገጫ ያሟላ፤

3/ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል ባለሙያዎች፣ ቴክኖሎጂ፣ የአሰራር ስርዓት እና ካፒታል፤

4/ በኢትዮጵያ ቋሚ አድራሻ፤ እንዲሁም

5/ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፍርድ ወይም በሕግ ችሎታውን ያላጣ፤

6/ ፈቃድ እንደሚሰጥበት የሳይበር ደህንነት አገልግሎት አስተዳደሩ በመመሪያ የሚያወጣቸው ዝርዝር መስፈርቶችን።

## 22. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታ

በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠዉ ማንኛዉም ሰዉ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ የተሰጠውን ፈቃድ ለተፈቀደለት ዓላማ እና ወሰን ብቻ የመጠቀም፤

2/ የተሰጠዉን ፍቃድ ለሦስተኛ ወገን በማናቸውም መልኩ አስተዳደሩን ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ ያለማስተላለፍ፤ ያለማዋስ፣ እንዲጠቀምበት ያለማድረግ፤

3/ የተሰጠውን ፈቃድ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ቦታ ወይም ቢሮ በግልፅ በሚታይበት ቦታ ላይ የማስቀመጥ፤

4/ ለፈቃዱ መሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች ላይ ለውጥ ሲኖር ለአስተዳደሩ ወዲያውኑ የማሳወቅ፤

5/ በስራ አጋጣሚ ያገኛቸውን መረጃዎች በሚስጥር የመያዝ፤

6/ በአስተዳደሩ የቁጥጥር ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት የሚጠይቃቸውን አስፈላጊ መረጃዎች የማቅረብና ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠት፤

7/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎች ማክበር፤

## 23. ፈቃድ ስለመሰረዝ

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰረዝ ይችላል፤

ሀ) ፈቃዱን ለማግኘት የቀረቡ መረጃዎች የተጭበረበሩ ወይም ሀሰተኛ ሆነው ሲገኙ፤

ለ) የተሰጠውን ፈቃድ ከተሰጠው ዓላማና ወሰን ውጪ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ስለመጣሱ ሲረጋገጥ፤

መ) የተሰጠው ፈቃድ የጊዜ ገደብ ሲያበቃና ሳይታደስ ሲቀር፤

ሠ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሞት ወይም በሕግ ወይም በፍርድ ችሎታውን ሲያጣ፣ ወይም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ሲፈርስ፣ በህግ መክሰሩ ሲረጋገጥ ወይም ሲዘጋ፤

ረ) ፍቃድ የተሰጠው ሰው በማጭበርበር፣ በማታለልና እምነት በማጉደል ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ሰ) ፈቃዱን ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ሲጓደል፤

ሸ) ባለፈቃዱ አገልግሎት መስጠቱን ሲያቋርጥ፤

ቀ) ሌሎች አስተዳደሩ በመመሪያ የሚለያቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ።

2/ አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከተሟሉ ፈቃዱን ይሰረዛል።

## 24. ፈቃድ ስለማገድ

አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 1 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ጥርጣሬ በሚኖርበት ወቅት ጉዳዩ እስኪጣራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፈቃዱ እንዲታገድ ሊወስን ይችላል።

## 25. ለባለሙያዎች እውቅና መስጠት

አስተዳደሩ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ውስጥ የሳይበር ደህንነት ተግባር ለሚያከናውኑ የሳይበር ደህንነት ባለሙያውችን እውቅና እና ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ስርዓት በመመሪያ ይዘረጋል።

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 26. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰው አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች የማክበርና የመተባበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

## 27. አስተዳደራዊ እርምጃ

1/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ፦

ሀ) አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን በወቅቱ ካልተገበረ፤ ከአምስት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር

ለ) የሚያጋጥሙ የሳይበር ጥቃቶች ለብሔራዊ ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል በወቅቱ ካላሳወቀ ወይም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ከአንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ እሰከ ሁለት ሚሊዮን ብር፤

ሐ) ብሔራዊ ድንገተኛ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል ለሳይበር ጥቃቶች ምላሽ ለመስጠት በሚያደርገው እንቅስቃሴ አስፈላጊ መረጃዎችን ካልሰጠ ወይም ተገቢውን ትብብር ካላደረገ፣ ከሦስት መቶ ሺህ እስከ ግማሽ ሚሊየን ብር፤

መ) በየጊዜው ለሚደረገው የሳይበር ደህንነት ኦዲት ተገቢውን ትብብር ካላደረገ፤ ከአንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ እስከ ሁለት ሚሊዮን፤

ሠ) በሳይበር ኦዲት የተገኙ ክፍተቶች ላይ አስተዳደሩ ማስተካከያ እንዲያደርግ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ በወቅቱ ካልወሰደ ከስምንት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር

ረ) የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ ያልተደረገባቸውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቶችን በማናቸውም መልኩ ከተጠቀመ፤ ከስምነት መቶ ሺህ ብር እስከ አንድ ሚሊየን ብር፤

ሰ) በዚህ አንቀፅ ከሀ እስከ ረ ከተደነገጉ ውጭ በአዋጁ አንቀጽ 7 እና 26 ላይ የተመላከቱትን ግዴታዎች ከተላለፈ ከአምስት መቶ ሺህ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን፣

የገንዘብ ይቀጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ 1 የተደነገገው ቢኖርም፤ የጥፋቱ ክብደት አነስተኛና፣ ጉዳት ያላደረሰ እንዲሁም በተደጋጋሚ ያልተፈፀመ ከሆነ አስተዳደሩ ተገቢው የእርምት እንዲወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊያልፈው ይችላል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የደረሰው ጥፋት በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ኑሮ፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ሰላምና መረጋጋት ላይ ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ አስተዳደሩ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በማሳወቅ ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያስደርጋል።

4/ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የሳይበር ደንነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ወይም በአንቀፅ 22 የተደነገጉ ግዴታዎችን ተላልፎ ከተገኘ ከብር አንድ ሚሊዩን ሁለት መቶ ሺህ ብር እስከ ሁለት ሚለዮን ብር ይቀጣል፤

5/ በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩ ጥፋቶችን ከአንድ ጊዜ በላይ የፈጸመ እንደሆነ ለጥፋቱ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን በሶስት እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል።

28. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

በሌሎች ህጎች የተደነገጉ ቅጣቶች ሆነው፤ ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ፣ በቸልተኝነት ወይም ተገቢውን ሙያዊ ጥንቃቄና ትጋት ሳያደርግ በዚህ አዋጅ የተጣሉ ግዴታዎች ሳይወጣ፡

1/ በቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ የሳይበር ጥቃት የደረሰ እንደሆነ እንደተሳትፎ መጠን እስከ አንድ አመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

2/ የደረሰው ጥቃት የቁልፍ መሰረተ ልማቱ አገልግሎት የሚያቋርጥ፣ የሚያስተጓጉል፣ ጉዳት ካደረሰ፣ ተዓማኒነት ካሳጣ ወይም ሚስጥራዊነቱ የተጋለጠ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር አምስት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

3/ የደረሰው ጥቃት ብሔራዊና ደህንነት፣ ብሔራዊ ጥቅም፣ በዜጎች ጤና እና ህይወት፣ ከባቢ አየር ላይ ቀውስ የሚፈጥር ከሆነ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር አንድ ሚሊየን እስከ ሦስት ሚሊየን በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል።

29. <u>ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

30. <u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፤

2/ አስተዳደሩ በዚህ አዋጅና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

31. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ................ ቀን 2016 ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት